# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 1 ቁጥር 34 መጋቢት 03 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ


# የወጣቱ ጥያቄ እና ተሳትፎ



# የወጣቱ ጥያቄ እና ተሳትፎ

ኢዜማ በመሪው በኩል የካቲት 18 ቀን 2012 ዓም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባስተላለፈው መልዕክት ለአገራችን ወጣቶች የሚከተለውን ጥሪ አድርጎ ነበር፦ ‹‹ከማንም በላይ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መፈጠር የሚጠቅመው እናንተን ነው። እኛ በወጣትነታችን ያደረግነውን ስህተት እንዳትደግሙ መጠንቀቅ አለባችሁ። በጊዜው በስሜት ተነድተን፣ በደንብ ያላላመጥነውን ርዕዮተ ዓለም እንደ ኃይማኖት ይዘን፣ የተገራ የመንግሥት ሥርዓት ለማቆም ሳይሆን ስሜታችንን በተቆጣጠረው የጊዜው ርዕዮት ተነድተን አገራችንን እስካሁን ልትወጣው ላልቻለችው መከራ ዳርገናታል። በዚህ ሂደት ከማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል ይልቅ እኛ ተጎዳን። ወጣት ወንድም እህቶቻችንን፣ የቅርብ ዘመዶቻችንንና ጓደኞቻችንን ገብረን አገሪቱን ለከፋ አምባገነናዊ ሥርዓት ዳረግናት። እናንተም አሁን የገጠማችሁን የህይወት ችግሮችና ከዚህም የመጣውን ብስጭታችሁን እየቆሰቆሱ የአጭር ግዜ ችግራችሁ ላይ አተኩራችሁ ዘላቂውን የአገራችንና የራሳችሁን ጥቅም እንዳታዩ ለሚጋርዱችሁ ኃይሎች መሳሪያ አትሁኑ! እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲፈጠርና ማኅበረሰቡ የሚቆጣጠረው መንግሥት ሴመሰረት፣ ሁላችንንም በእኩልነት የምታስተናግድ አገር ስትኖረን ብቻ ነው የናንተም ሆነ የሁላችንም ኢትዮጵያዊያን መሰረታዊ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ ማግኘት የሚችሉት ።››

የአገራችን ፖለቲካ ፓርቲዎች በአብዛኛው በእድሜ የሕዝቡን ወጣት ክፍል እንደማይወክሉና ስለ ወጣቱ መናገር እንጂ ወጣቱን የማነጋገር ልማድ እንዳላዳበሩ ይታማሉ። የዚህ አጭር ጽሁፍ ዓላማ ኢዜማ ለወጣቱ የአገራችን ክፍል ያለውን ራዕይ ማስረዳትና በመሪያችን በኩል ለተላለፈው ጥሪ ተጨማሪ አጽንዖት መስጠት ነው።

ጥቂት ዓመታት ያስቆጠረውን የሕዝብ ቆጠራ በመመርኮዝ የተደረጉ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) እና የሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማት ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከ75 በመቶ በላይ የሆነው የአገራችን ሕዝብ ከ24 ዓመት በታች እንደሆነ ይገመታል። ከ75 ሚልየን በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ1 ወር እስከ 24 ዓመት ያክል ቢሆነው ነው እንደማለት ነው። የምርጫ ቦርድ ባደረገው ስሌት መሰረት እንዳስታወቀው ደግሞ ከአገራችን ሕዝብ 52% ያህሉ መምረጥ በሚችልበት እድሜ ክልል ወይም ከ18 ዓመት በላይ ነው። የተለያዩ ጥናቶችን በማመሳከር እንዳሰላነው ከሆነ ከመራጩ ሕዝብ መካከል ከ10 ሚልየን ሕዝብ የማያንሰው ከ18 እስከ 24 ዓመት የዕድሜ ክልል ወስጥ እንደሚገኝና ከ4 እስከ 5 ሚልየን የሚሆኑት ወጣት ሴቶች እንደሆኑ ኢዜማ ይገምታል።

## ወጣቱ የሚገኝበት ሁኔታ

ወጣት የሚባለው የአንድ አገር ሕዝብ አካል እንደየአገሩ የባሕልና የኢኮኖሚ አውድ ይለያያል። ለምሳሌ በምዕራብ አገራት ወጣት የሚባለው ከ18 እስከ 24 ዓመት እድሜ ክልል ያለው ሕዝብ ሲሆን  አገራችን ያጸደቀችው የአፍሪካ የሰብዓዊና የሕዝቦች መብት ስምምነት ወጣት ማለት ከ18 እስከ 40 ዓመት መካከል የሚገኘው የሕዝብ ክፍል እንደሆነ ይደነግጋል። የአገራችን ‹‹የወጣቶች ጉዳይ ፖሊሲ›› ለመጨረሻ ግዜ የተሻሻለው ከዛሬ 16 ዓመት በፊት በ1996 ዓም ሲሆን ወጣት ማለት ከ15 እስከ 29 ዓመት የእድሜ ክልል ያለ ሰው ነው። ( https://www.youthpolicy.org/fact-sheets/country/ethiopia/ ) በተጨማሪም የሕጻናት፣ የሴቶችና የወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ድረገጽ ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲውን የሚያስረዳ አጭር ሰነድና ‹‹የገጠር ወጣቶች የእድገት ፖሊሲ›› መቀረጹን ይገልጻል።

ወጣት የሚባለውን የሕዝብ አካል በግልጽ መለየትና በአኃዝ በሚገባ ማስቀመጥ የተለያዩ ወጣት ደጋፊ ፖሊሲዎችን ለማጽደቅ እንዲሁም የአንድን አገር ኢኮኖሚ ገቢ አመንጪ የሰው ኃይል ለመገመት ወይም ከዚህ ጋር የሚያያዙ የጡረታ፣ የትምህርት ወይም የጸረ ሱስና ጸረ ወንጀል ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ አስፈላጊ ነው። በአገራችን ወጣቱን በተመለከተ ያለው መረጃ በጣም አናሳ ነው። በቅርብ ግዜ የሕዝብ ቆጠራ አልተካሄደም እንዲሁም ወጣቱን በተመለከተ ያሉት ጥናቶች በጥቂት ናሙናዎች ላይ የተመሰረቱና በአብዛኛው በዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተደረጉ ናቸው። ይህንን የመረጃና የጥናት እጥረት መሙላትና የወጣቶችንና የሕጻናትን ጉዳይ የሚከታተሉ መዋቅሮችን ማጠናከር፣ በተለይም በየክልሉና ወረዳው ተወካይነት እንዲኖራቸው ማድረግ ቀዳሚ ተግባር መሆን እንዳለበት ኢዜማ ያምናል። ስለሆነም የአገራችን ሕዝብ ቁጥር እና የወጣቱ ክፍል ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩ በእራሱ የሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳዮችን በአሁኑ ወቅት ከሚተዳደርበት አንድ ሚኒስቴር ሥር የሕጻናትና ወጣቶች ጉዳዮችን ነጥሎ የሚከታተል ሚኒስቴራዊ መዋቅርን አስፈላጊነት መልሶ ለመፈተሽ በቂ ምክንያት እንደሆነ ኢዜማ ያምናል። በማያያዝም የአገራችን የወጣት ትርጓሜ ማሻሻል አስፈላጊነት ከነዚህ ጥናቶችና የመዋቅር ለውጦች አኳያ እንዲሁም አገራችን ካጸደቀቻቸው የተለያዩ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች አኳያ የሚገመገም ይሆናል።

ለግዜው በተጠቀሱት የአገራችን የወጣቶች ጉዳይ ፖሊሲዎችና ሌሎች በቅርብ ግዜ በተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተደረጉ ጥናቶች መሰረት

- ከ15 እስከ 29 እድሜ ክልል የሚገኘው የአገራችን ሕዝብ 22 ሚልየን ገደማ ይሆናል (2003 ዓ.ም)
- ከዚህ መካከል 16 ሚልየን የሚሆነው ‹‹በገጠሩ›› የአገራችን ክፍል የሚኖር ነው
- ከግማሽ በላዩ ሴቶች ናቸው
- በአብዛኛው (ከ68 በመቶ በላይ) ማንበብ እና መጻፍ የሚችል ነው
- በአብዛኛው ‹‹ሥራ አጥ›› ወይም ቋሚ ሥራ የሌለው ነው
- ሙያዊ ሥልጠና የሚያገኝበት እንዲሁም ከተለያዩ ሱሶች ነጻ የሆኑ መዝናኛ ቦታዎች የሉትም
- ስደት እና ኤች አይ ቪን ጨምሮ ለተለያዩ በሽታዎችና ማኅበረሰባዊ ቀውሶች የተጋለጠ ነው።

ይህ እንዳለ ሆኖ በጥናት እና መረጃ ላይ ሳይሆን በግምት ወይም በሃሜት ደረጃ በስፋት እንደሚታመነው ከሆነ ወጣቱ የአገራችን ክፍል

- ከ2 ወይም 3 በመቶ በማያልፈው የአገራችን ኢንተርኔት ተጠቃሚ ሕዝብ አብዛኛውን ድርሻ የያዘ እና ኢንተርኔትንም በብዛት ለማኅበራዊ ሚድያ የሚጠቀም፣
- በተለያዩ ወንጀሎችና ሱሶች የተጠመደ እንዲሁም ከአገራዊ ጉዳዮች ይልቅ በዋዛ ፈዛዛ እና ገንዘብ ማግኛ አቋራጮች በማፈላለግ ጊዜውን የሚያጠፋ፣
- የንባብ ባህሉ እና በስፖርታዊም ሆኑ በሌሎች ክህሎቶች የተዳከመ፣
- ለሃሰተኛና ለጥላቻ ወሬ፣ ጽንፈኝነትና የኃይል እርምጃ ለሚሰብኩ ግለሰቦች በቀላሉ የሚታዘዝና በአጠቃላይ ለአገራችንም ሆነ ለሕዝቡ የሚያሰጋ አካል መሆኑ ነው።

ኢዜማ እነዚህና የመሳሰሉ ወጣቱን በተመለከተ ያሉ እምነቶች የተዛቡና ወጣቱን በጅምላ የሚወነጅሉ መሆናቸውን ይረዳል። በአንጻሩ እንደ ኢዜማ ጽኑ እምነት ወጣቱ የአገራችን ክፍል በአገራችን ፖሊሲዎችና መዋቅሮች የሚገባው ክትትል ያልተደረገለት፣ በትምህርት ጥራት እጦት ምክንያት ተገቢውን ክህሎትና እውቀት ያላገኘ እንዲሁም በአገራችን በነበረው የመልካም አስተዳደር እጦት ያስከተላቸውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች በአጠቃላይ ከማንኛውም የሕዝባችን አካል በላይ ያስተናገደ መሆኑን ነው።

## የወጣቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ምንድነ ነው?

የወጣቱን መሰረታዊ ፍላጎት ለማወቅ የተደረገ አገር አቀፍና ጥልቅ የሆነ ጥናት በሌለበት ሁኔታ እያንዳንዱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆነ አካል ወይም የፖለቲካ ፓርቲ የራሱን መላምት ወይም ወካይ ባልሆነ ናሙና ላይ በተመሰረተ እይታ አንጻር ድምዳሜ መውሰዱ የማይቀር ነው። በኢዜማ በኩል ምን ጥረት ተደርጓል ለሚለው ምላሹ ቢያንስ እስካሁን ፓርቲያችን ባደረጋቸው እንቅስቃሴዎችና አደረጃጀቶች በተቻለ አቅም አካባቢያቸውን የሚወክሉ ወጣቶችና ሴቶች ማሳተፍና ማካተት ዋነኞቹ ናቸው። ፓርቲያችን በማኅበራዊና በሌሎች መገናኛ ብዙኃን ለሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ከፍተኛውን አስተዋጽዖ/በአስተያየትና በመሳሰሉት መልክ ተሳትፎ የሚያደርጉት በአብዛኛው ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ነው።

በእነዚህና ከወጣቱ ጋር በሚያገናኙን ሁለትዮሽ መስመሮች የተረዳነው የወጣቱ ዋና ጥያቄ በአገሩ ላይ በክብርና መሰረታዊ ፍላጎቱን ሊያሟላ የሚችል ገቢ አግኝቶ መኖር ነው (decent & dignified living)። የክብርና የመሰረታዊ ፍላጎትን የሚያሟላ ኑሮ ጥያቄ የሰብዓዊ መብት ጥያቄዎች ናቸው፣ ወጣቶች ይህንን መጠየቅ መብታቸው ነው፣ በዜግነታቸው እንዲሁም ሰው በመሆናቸው ሊያገኙት የሚገባ መብት ነው። አንድ ወጣት በጾታ፣ በብሔር፣ በአካባቢ ወይም በአካላዊ ጤንነት መድልዎ ሳይደርስበት የአዋቂነት እድሜ ሲደርስ (18 ዓመት ሲሞላው) በፈለገው ሙያ ወይም የገቢ ምንጭ ሊያሰማራው የሚችል ትምህርት ወይም ሥልጠና የማግኘት፣ በሙያው መተዳደር፣ እራሱን የሚችልበት ገቢ የማግኘት፣ በገቢው መጠን መጠለያና ሌሎች መሰረታዊ ልማት አገልግሎቶችን የማግኘት መብት አለው። የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወጣት ቀዳሚ ምርጫ በገዛ አገሩ የግልና የማኅበራዊ ሕይወት ራዕዩን ነድፎ መተግበር የሚያስችለው እምነት ማግኘት ነው።

ዛሬ በአገራችን ያለው እውነታ ግን የተለየ ነው።

- ወጣቱ እነዚህን ጥያቄዎች በሰላማዊ መንገድ የሚገልጽበትና አቤቱታ የሚያሰማበት መድረክ ከመነፈጉም ባሻገር የመደራጀት፣ በሲቪክ ማኅበራት መልክ የመንቀሳቀስ፣ የመሰብሰብ፣ በጽሑፍና በፕሬስ ሃሳቡን የመግለጽ መብቶች በሙሉ ታፍነው እነዚህን የመሳሰሉ እንቅስቃሴዎች ማድረግ ለከፍተኛ እስር፣ ስቃይና እንግልት የሚያጋልጡ ሆነው ቆይተዋል።
- በመንግሥት በኩል ሆን ተብሎ በሚደረግም ሆነ ባለማወቅ የወጣቱ ክህሎትና እውቀት ደረጃ ማነስ የወጣቱ ጥፋት ወይም እንዝህላልነት ውጤት አድርጎ ማቅረብ፣ ወጣቱን በአደገኛ ቦዘኔና በሽብርተኝነት በጅምላ መፈረጅ እንዲሁም ወጣቱ እርዳታ ፈላጊ ወይም ተቀባይ ብቻ ተደርገው ይቀርቡ ነበር።
- የመንግሥት ባለሥልጣኖችና

## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢ-ሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

መጋቢት 03 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

መንግሥትን የሚደግፉ ግለሰቦችና አካላት በፍጥነትና ሕገወጥ በሆነ መንገድ የተለየ አገልግሎት ሲያገኙ፣ የተለያዩ ዲግሪና ዲፕሎማዎችን ሲታደሉ፣ በመንግሥት ሚድያዎች በሙሉ በሥራ ፈጣሪነት፣ በልማታዊ ገበሬነት ወይም በመሳሰሉ ሲሸለሙ እንዲሁም የቅንጦት ኑሮ ሲኖሩና ገንዘብ ሲያካብቱ በመቆየታቸው በወጣቱ ላይ የላብና የድካም ውጤት ላይ እንዲሁም በአገሩ ማኅበራዊ ፍትሐዊነት ላይ እምነት ማጣት አድሯል።

እነዚህ የመብት ረገጣዎችና የመልካም አስተዳደር እጦቶች በተራቸው በተለይ ወጣቱ ክፍል ላይ የሚያስከትሏቸው በርካታ ስነ ልቦናዊ ጫናን ጨምሮ ሌሎች ችግሮች አሉ። ለምሳሌ ያህል መንግሥትን ከመደገፍ ውጪ ወጣቱ እራሱን የሚያስችለው ሕይወት ለመኖር ያለው አማራጭ ከአገር መውጣት ወይም ለአካላዊና ለጉልበት ብዝበዛ መዳረግ እንዲሆን፣ በአገሩ ኢኮኖሚያዊም ሆነ ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ ማለት ከፍተኛ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ከመሳተፍ እኩል አደገኛ እንደሆነ ወይም ማንኛውንም በአካባቢው ላይ የሚያየውን ማኅበራዊ ጉዳይ ለማገዝ የሚያስችል ትንሽ እንቅስቃሴ ለማድረግ መንግሥትን መደገፍ ግዴታ እንዲሆንና እና መሰረታዊ የመብት ጥያቄ ማንሳት ከሚያስከፍለው ከፍተኛ መስዋትነት የተነሳ መብት መጠየቅ ‹‹የጥቂት ጀግኖች›› ‹‹ድፍረት/ጀብደኝነት›› እንዲሆን ተደርጓል።

የነዚህ እምነት ማጣቶች ድምር ወጣቱ ከአገሩ ጋር ከሚያስተሳስሩት የአስተዳደር፣ የኢኮኖሚ፣ የፍትሕ መዋቅሮችና ተቋማት ጋር እንዲሁም ሽምግሌዎችና የአካባቢ መሪዎች ካሉ ባሕላዊና ማኅበረሰባዊ ተቋማት ያለው የእውነተኛ ለውጥ አምጪነትና ትርጉም ላይ ጥርጣሬ እንዲኖረውና ከተቋማቱ ጋር ያለው ግንኙነት እንዲላላ ብሎም እንዲበጠስ አድርጓል። በዚህ ሁኔታ ወጣቱ የመብት ጥያቄውን ከማን አለብኝነት ጥያቄ ወይም ሰላማዊውን መንገድ ከጉልበተኛ መንገድ መለየት የሚያስችሉትን ማጥለያዎች (በማኅበራዊ ሳይንስ "social filters" የሚባሉትን) ስለሚያጣ ወጣቱ ያለው አማራጭ ሃሳቡንና ጥያቄዎቹን መግለጽ የሚቻለው በ"ጀብደኝነትና" (heroics) በኃይል ብቻ ነው ብሎ ቢያምን የሚያስገርም ሊሆን አይችልም።

## የወጣቱ ጥያቄዎች ያገኛቸው ምላሾች

ወጣቱ በክብርና መሰረታዊ ፍላጎቶቹ በተሟሉለት ሁኔታ የመኖር መብት ጥያቄውን ግልጽ በሆነና ወጣቱ እራሱም ሆነ ሌላው ኅብረተሰብ በቀላሉ ሊረዳው በሚችል መልኩ መገለጹ ጥቅማቸውን በሚነካባቸው ወይም አቅም በሌላቸው አካላት/ቡድኖች መጠቀሚያ ሲሆን ቆይቷል።

> **" የአገራችን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሳያግዱት ወጣቱ ለእራሱ የመብት ጥያቄ እራሱ የሰጠው ምላሽ ይበልጡን ውጤት አምጥቶለታል እንዲሁም የወጣቱን ተነሳሽነትና የፈጠራ ችሎታ በግልጽ አሳይቷል። "**

በአንድ በኩል መሰረታዊ የመብት ጥያቄዎቹን ልዩ ልዩ አወዛጋቢና አወናባጅ መልክ ሸፍነው በማቅረብ ግዜያዊም ቢሆን በቁጥር ብዛትና በስሜት የተቆጣ ትኩስ ወጣት ኃይል በወቅታዊም ሆነ በቋሚነት ማሰባሰብ የሚፈልጉ በዋናነት ሶስት አይነት ቡድኖች አሉ።

- አንደኛ እንደዚህ ዓይነት ኃይል ማሰባሰብ የመንግሥት ሥልጣን ለማግኘት ወይም ይዞ ለመቆየት አቋራጭ መንገድ ነው ብለው የሚያስቡ፣
- ሁለተኛ አገራችንን ለረጅም ግዜ ያልተረጋጋና ሰላም በሌለው ሁኔታ በማቆየት የተለየ የገንዘብ ጥቅም የሚያገኙና
- በሶስተኛነት በቡድንም ሆነ በግል ደረጃ ከ‹‹ቡድን መሪነት›› ውጪ በክህሎትም፣ በእውቀትም እና አማራጭ ሃሳብ በማምጣትም ምንም የገቢና የመተዳደሪያ ምንጭ ወይም መወዳደሪያ አቅም የሌላቸው ናቸው።

በነዚህ ዓይነት ቡድኖች የተነሳ እውነተኛና ተጨባጭ ማስረጃ ሊቀርብባቸው የሚችል ብሔርን፣ አካባቢን፣ ጾታን ወይም አካላዊ ጤንነትን መሰረት ያደረጉ ጭቆናዎች ተዓማኒነት እንዲያጡ ተደርገዋል፣ በጥቂት የፖሊሲ ማሻሻያዎች ሊታረሙ የሚችሉ ጉድለቶች አወዛጋቢና በሕዝብና በተመሳሳይ ዕድሜና ስቃይ ውስጥ በሚገኙ ማኅበረሰቦች መካከል ቁርሾ የሚጥሉ ጉዳዮች ሆነው እንዲከርሙ ተደርገዋል። እንዲሁም በተለይ ወጣቱ ላይ በእራሱ አቅምና በማንነቱ ላይ እንዲሁም በአጠቃላይ በሰላማዊ መንገድ ላይ ፍጹም ተስፋ እንዲቆርጥ አድርገዋል።

በሁለተኛ ወገን ደግሞ መንግሥት በውጪም ሆነ በውስጥ ተጽዕኖ ወይም ግፊት የሚወስዳቸው እርምጃዎች የአገራችንን የመልካም አስተዳደር ችግሮች የድኅነት ወይም የልማት እጦት (ወይም የ‹‹ዳቦ ጥያቄ››) አድርጎ በመቁጠር አባዜ የተቀረጹ በመሆናቸው ለወጣቱ ችግር ተመጣጣኝ ምላሽ መስጠት አለመቻላቸው ነው። የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሲያምጽ በዩኒቨርሲቲ ምግብ ጥራት የተነሳ እንደሆነ አድርጎ ማቅረብ፣ በከፍተኛ ቁጥር ስደተኛ አመንጪነት አገራችን ስትታማ የወጣቶች የብድር ፈንድ ማስመረቅ፣ የሥራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ የ‹‹ኮብል ስቶን›› ፋብሪካ መክፈት ወይም የትምህርት ጥራት መዝቀጥ ሲታማ የ70-30 ድልደላ ፖሊሲ መንደፍ የመሳሰሉት እርምጃዎች መንግሥት በወጣቱ መሰረታዊ ችግር ላይ የሚያፌዝ አስመስሎታል። ወጣቱ ከመንግሥት ፖሊሲዎች ያገኘው ምላሽ የሰብዓዊ መብት ጥያቄዎቹን አልመለሱም። በስደትም ሆነ በአገር ውስጥ የሚያጋጥመውን ዓይነት ጉልበቱንም ገብሮ ኑሮውን የማይለውጥለትና እራሱን የማያስችለው ገቢ ማግኘት የጉልበት ብዝበዛና የሰብዓዊ መብት ጥሰት ነው፣ የመንግሥትን ኮታ ለማሟላት ወጣቱ ባልመረጠው ሙያ ቢደለደል የሰብዓዊ መብት ጥሰት ነው...... ወዘተ ወዘተ።

ይልቁን በእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ውስጥ ወይም እነዚህ የአገራችን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሳያግዱት ወጣቱ ለእራሱ የመብት ጥያቄ እራሱ የሰጠው ምላሽ ይበልጡን ውጤት አምጥቶለታል እንዲሁም የወጣቱን ተነሳሽነትና የፈጠራ ችሎታ በግልጽ አሳይቷል። በ1997 ዓ.ም ምርጫ ወቅት ሆነ ከዛ በኋላ በታዩ እንደ በአረብ አገር ለሚሰቃዩ እህቶቻችን የተደረገውን እና በሊቢያ ለተሰዉ ወጣቶች ጉዳይ ለቀሰቀሰው ሕዝባዊ ተቃውሞ ዓይነት ያሉ እንዲሁም እንደ ቆሼ መደርመስ ላስከተለው የሰው ሕይወት መጥፋት ዓይነት ያሉ በተለያየ አጋጣሚ ለሚያስፈልጉ ሕዝባዊ ንቅናቄዎች ዋነኛ አስተባባሪና ተሳታፊ ወጣቱ የአገራችን ሕዝብ ነበር። የተለያዩ የአገራችንን በዓላትን ለማሰብና ለማክበርም ሆነ ለመሬት መፈናቀል ጥያቄ ዛሬም እንደትላንቱ ግንባር ቀደም ተሰላፊ ወጣቱ ነው። ወጣቱ ከማንም ተቋም ወይም ቡድን ሥልጠና ሳያስፈልገው የማኅበራዊ ሚድያውን ጥቅምና አገልግሎት ተረድቶ በተግባር ለበርካታ መልካም አገልግሎቶችና ለዴሞክራሲ ትግል ያዋለ እንዲሁም ሁሉም ሰላማዊ ሃሳብን የመግለጫ መንገዶች በተዳፈኑበት ወቅት ሃሳቡን በሥነ ጥበብ ፈጠራው መግለጽ የቻለ ኃይል ነው።

ባለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት ውስጥ በሁሉም የአገራችን ክፍሎች ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተካሂደዋል፣ እነዚህን ጥሰቶች የእራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ደኅንነት አደጋ ላይ በመጣል ይፋ ያወጡ፣ የተቃወሙ፣ በመቃመዋቸው ለእስር፣ ለስቃይ፣ ለሞትና ለስደት የተዳረጉ ግለሰቦችና ቡድኖች በሙሉ ወጣት በምንለው የእድሜ ክልል የሚገኙ ነበሩ። የትግል አማራጭን ለወሰኑ የፖለቲካ ኃይሎችም ሆነ በአገር ውስጥ ለተካሄደው የእምቢተኝነት እንቅስቃሴ እራሳቸውን አሳልፈው የሰጡት የኢትዮጵያ ወጣቶች ናቸው። ዛሬ አገራችን ላነገበችው የዴሞክራሲ ተስፋ ጭላንጭል ውለታው የወጣቱ ነው።

## ለወጣቱ ዛሬ ምን አማራጭ አለ?

ወጣቱ የአገራችን ክፍል እንደ ቡድንም ሆነ እያንዳንዱ ወጣት እንደግለሰብ ከየትኛው የሕዝባችን ክፍል በበለጠ መብትና ግዴታውን የሚያውቅ፣ ሌሎች አገራት የደረሱበትን የኢኮኖሚና የእድገት ደረጃ የሚናፍቅ፣ አገራችን በአካባቢዋ ላይም ሆነ በውስጧ የተጋረጠባትን ውስብስብ ችግሮች ጠንቅቆ የሚረዳ አካል እንደሆነ ኢዜማ ያምናል። ወጣቱ ከእናትና ከአባቶቹ ታሪክ የመነጨ ሥነልቦናዊ ጥንካሬና አገራዊ ስሜት፣ የሉዐላዊነትና የክብር ከፍተኛ ትርጉም የተረዳና ለአገራዊ ጥሪ ከያለበት የሚሰባሰብ ኃይል እንደሆነ በተደጋጋሚ አሳይቷል። የኢትዮጵያ ወጣት ስብዕናና ጠንካራ ማንነት በጥቂት ወቅታዊ ሁኔታዎች በጅምላ የሚፈረጅ ወይም የሚወከል አይደለም።

እንዲሁም ኢዜማ በየትኛውም የአገራችን ክፍሎች የሚገኙ ወጣቶች ቀዳሚ ጥያቄ በክብርና መሰረታዊ ፍላጎቶቹን የሚያሟላ ኑሮ የመኖር የመቻል ጥያቄ እንደሆነ ያምናል። ወጣቱ መብቱን የመጠየቅ፣ ሃሳቡን በሰላማዊ መንገድ መግለጽ የሚችልበት መድረክ ሲያጣ አቤቱታ ለማሰማት የሚቀረውን አማራጭ አይቷል፣ ተጎድቷል፣ በእምቢተኝነት ታግሎታል። መልሶ ይህንን ዓይነት አስተዳደር በዝምታ ይቀበላል ብሎ ማመን ወጣቱን አለመረዳት ብሎም መናቅ ነው። እንዲሁም ያለፉት መንግሥታት እንዳደረጉት ሁሉ የወጣቱን ሰብዓዊ መብት ጥያቄ የብሔር፣ የዳቦ፣ የሥልጣን ወይም በሌላ ሁለገብ ባልሆነ መልኩ ተርጉሞ ምላሽ ለመስጠት መሞከርም እንዲሁ ወጣቱን ለተጨማሪ የመስዋትነት ፍዳ መዳረግ ነው።

የወጣቱን የክብርና የመሰረታዊ ፍላጎት ማሟላት የሚያስችል ኑሮ ጥያቄ ለመመለስ በመጀመሪያ በአገራችን መልካም አስተዳደር መስፈን እንዳለበት እናምናለን። መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ወጣቱም ሆነ ሌላው የሕዝባችን አካል እርሱን የሚመስለውን፣ ችግሩን አብሮ የተጋራውን፣ ቅሬታ ቢያቀርብ ተጠያቂ ሊያደርገው የሚችለውን አካል አወዳድሮ በምርጫው መወከል ሲችል ብቻ ነው። መልካም አስተዳደር ካልሰፈነ የወጣቱ ጥያቄ በእኩልነት ወይም በዜግነት ሳይሆን በብሔር፣ በጾታ፣ በአካባቢ፣ በአካላዊ ጤንነት በቋንቋ ወይም በዝምድናና በመሳሰሉ መድሎዎች የሚገመገም ሆኖ ይቀጥላል። ወጣቱ ይወክለኛል፣ ነገ ሳልሳቀቅ ቅሬታ ላቀርብበት እችላለሁ የሚለውን አካል ካልመረጠ አሁንም ለጥያቄው ተመጣጣኝ ምላሽ አያገኝም።

ስለዚህ ዛሬ ወጣቱ በቅድሚያ ለኑሮው፣ ለቤተሰቡ፣ ለአካባቢው እና ለአገሩ ያለውን ምኞትና ራዕይ የሚያንጸባርቅና በየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ቢሆን ምላሽ ሊሰጠው የሚችለው ጥያቄ ምን እንደሆነ በግልጽ ሊረዳ ይገባል። በሁለተኛ ደረጃ ሁሉም የአገራችን ክፍል ተዓማኒና ፍትሐዊ ነው ብሎ ሊያምንበት በሚችል ሂደትና መልክ ጥያቄውን ተቀብሎ ተመጣጣኝ ምላሽ ሊሰጠው የሚችለውን አካል ወጣቱ በበኩሉ ማወዳደርና ማማረጥ መቻል አለበት። አንዱ የአገራችን ወጣት ክፍል ጥያቄ ተመልሶ የሌላው ቢተው ወይም የአንዱ የአገራችን ወጣት ክፍል ጥያቄ የተመለሰው በተለየ መድልዎ ከሆነ ማኅበራዊ ፍትሐዊነቱ ይዛባል፣ በዜጎችም መካከል መበላለጥ ይሰፍናል።

ኢዜማ ለአገራችንም ሆነ ለወጣቱ ያለውን በዜግነት ላይ የተመሰረተ ማኅበራዊ ፍትሕ የማስፈን ራዕይ ለማሳካት ብቸኛው አማራጭ ፓርቲ ነው የሚል አቋም ፈጽሞ የለውም፣ ለየትኛውም ቡድንና ፓርቲ እንደዚህ ዓይነት እምነት አደገኛ እንደሆነ ያሳስባል። ለፓርቲያችን ያለን ራዕይ ፓርቲያችንን ከአመራሮቹ እድሜና የትግል ጉዞ በላይ ለረጅም ዓመታት የሚቆይና የሚያሻግር፣ ለአገራችን ያለውን ራዕይ በግልጽ ማስቀመጥና መቅረጽ የሚችል፣ በጥናት በመረጃ የሚያምን በለት ተዕለት እንቅስቃሴዎቹ በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ውሳኔዎችን አስተላልፎ መተግበር የሚችል ተረካቢ አባላትና ትውልድ መቅረጽ ነው። ፓርቲያችን ለመጪው ምርጫ ያለው ራዕይ ደግሞ የምርጫውን ውጤት ሁሉም ተሳታፊና ባለድርሻ አካላት ሊቀበሉት በሚችሉት መንገድ ሂደቱ ፍትኃዊ እንዲሆንና ለዚህም የበኩሉን አስተዋጽዖ ማድረግ ነው።

ጥሪያችንን በቅድሚያ ለወጣቱ የምናደርገው ወጣቱ በሕዝብ ቁጥር ብዛትም ሆነ በሚጫወተው ሚና የመጪው ምርጫ ሂደት ዋነኛው ተዋናይ እንደሆነ በፓርቲያችን ውስጣዊም ሆነ ሕዝባዊ እንቅሳቄሳያችን ስለተገነዘብን ነው። ጥሪያችንን በቅድሚያ ለወጣቱ የምናደርገው የምርጫው ሂደት ተዓማኒነት ዋነኛ ተጠቃሚ ወይም ተጎጂ የሚሆነው ወጣቱ የሕዝባችን አካል ስለሆነ ነው። ጥሪያችንን በቅድሚያ ለወጣቱ የምናደርገው ወጣቱ ያመጣውን የዴሞክራሲ ተስፋ ወጣቱ እንዳይቀለብሰው በመስጋት ነው፣ ታጋይ ቢሞትም ትግል ስለማይሞት ነው።

# ኢዜማ በቀድሞ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሕንፃ ላይ ዋና ጽሕፈት ቤቱን ከፈተ

የዜጎች መድረክ (መጋቢት 03 ቀን 2012 ዓ.ም)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ቀደም ሲል በሰማያዊ፣ በኢዴፓ፣ በመኢዴፓ፣ በአርበኞች ግንቦት 7 እና በሌሎች የከሰሙ ፓርቲዎች ስም ተመዝግበው የሚገኙ ጽሕፈት ቤቶቹን ለፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን በማስረከብ ዋና ጽሕፈት ቤቱን ወደ ስቴዲየም አካባቢ ማዘዋወሩን የፓርቲው ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

ፓርቲው ከዚህ ቀደም በጽሕፈት ቤት ጥበት ምክንያት የተለያዩ የሥራ ክፍሎችን በአንድ ቦታ ሰብስቦ ማሠራት አለመቻሉ የፈጠረውን ችግር ለመቅረፍ ሁሉንም የሥራ ክፍሎች አንድ ላይ መያዝ የሚችል ጽሕፈት ቤት እንዲሰጠው ለፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ከምስረታው ማግስት ጀምሮ ጥያቄ አስገብቶ ምላሽ ሲጠባበቅ መቆየቱን ሊቀመንበሩ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ፓርቲው አዲሱ ጽሕፈት ቤቱን ከፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ጋር መጋቢት 01 ቀን 2012 ዓ.ም ውል በመፈፀም በኪራይ መረከቡንና ከዚህ በኋላም በአዲሱ ጽሕፈት ቤት ሁሉም የሥራ ክፍሎች በአንድ ቦታ ሆነው ሥራዎቻቸውን እንደሚያከናውኑ ሊቀመንበሩ ጠቁመዋል፡፡ አዲሱ የፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት ከጊዮን ሆቴል ወረድ ብሎ ከሚገኘው ሀድያ ሱፐር ማርኬት ጎን ባለ የቀድሞ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሕንፃ ላይ ይገኛል፡፡

ኢዜማ ከዋና ጽሕፈት ቤቱ በተጨማሪ በአዲስ አበባ ከተማ በ23ቱም የምርጫ ወረዳዎች እንዲሁም በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች በሚገኙ 276 የምርጫ ወረዳዎች ላይ ቢሮዎችን ከፍቶ በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡

# ኢዜማ እጩ ሆነው መወዳደር ለሚፈልጉ ሰዎች በሩ ክፍት መሆኑን ገለፀ

የዜጎች መድረክ (መጋቢት 03 ቀን 2012 ዓ.ም)

የእጩዎች ምልመላና ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ ኢዜማን ወክለው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ሆነ ለክልል ምክር ቤት የሚወዳደሩ እጩዎችን የመመልመል ሥራውን እየሠራ እንደሚገኝና ኮሚቴው ያወጣቸውን መስፈርቶች የሚያሟሉ ማንኛውም እጩዎች ኢዜማን ወክለው እንዲወዳደሩ ኢዮብ መሳፍንት ጥሪ አቀረቡ፡፡

ለእጩ ተወዳዳሪነት ኮሚቴው ያወጣውን መስፈርት የሚያሟሉ እና ኢዜማን ወክለው ለተወካዮች ምክር ቤትም ሆነ ለክልል ምክር ቤት መወዳደር ለሚፈልጉ ሰዎች ኢዜማ አሁንም በሩ ክፍት መሆኑንና እጩ ሆነው መወዳደር የሚፈልጉ ሁሉ የምርጫ ወረዳዎቻቸውንም ሆነ ማዕከሉን በማነጋገር መረጃ ማግኘት እንደሚችሉ ኢዮብ መሳፍንት አስረድተዋል፡፡ በየምርጫ ወረዳው እጩዎችን የሚያወዳድሩ 5 አባላት ያሉት አስመራጭ ኮሚቴ የተዋቀረ ሲሆን አስመራጭ ኮሚቴዎች የእጩዎች ምልመላና ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ ያወጣውን መስፈርት በመንተራስ ለውድድር ብቁ ናቸው ያሏቸውን እጩዎችን ለይተው የሚያቀርቡ ይሆናል፡፡

መስፈርቶቹ ምን ዓይነት እጩዎች ያስገኙልናል ብላችሁ ትጠብቃላችሁ ስንል የእጩዎች ምልመላና ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ አባል የሆኑትንና የኢዜማ ምክትል መሪ የሆኑትን አንዱዓለም አራጌ የጠየቅናቸው ሲሆን በምላሻቸውም በተቻለ መጠን መስፈርቶቹ ከአባላቶቻቸው ውስጥ ሕዝቡ የሚያከብረውን፣ በተሻለ የሚሠራውንና ፓርቲያቸውን በተሻለ የሚወክለውን ሰው እጩ ሆነው ከሚቀርቡት ሰዎች መሀል ለመለየት እንደሚረዳቸው ገልፀዋል፡፡

እጩዎችን የመመልመሉ ሥራ እንዳልተጠናቀቀና እጩ ሆነው መመዝገብ የሚፈልጉ ሰዎች በየወረዳዎቻቸው ለሚገኙ አስመራጭ ኮሚቴዎች ሰነዶቻቸውን እስከ መጋቢት 14 ቀን 2012 ዓ.ም ማቅረብ እንደሚችሉ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡

## ‹‹ወጣቶች ከአድዋ ድል ከፍ ያለ ዴሞክራሲን የማዋለድ ሥራ መደፋቸው ውስጥ ወድቆ ይገኛል›› አንዱዓለም አራጌ የኢዜማ ምክትል መሪ

የዜጎች መድረክ (መጋቢት 03 ቀን 2012 ዓ.ም)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ምክትል መሪ አንዱዓለም አራጌ የኢዜማ ወጣቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ የፊታችን እሁድ መጋቢት 06 ቀን 2012 ዓ.ም የሚያካሄደው የወጣቶች ኮንፍረንስ ላይ ወጣቶች እንዲገኙ ጥሪ አቀረቡ፡፡

ምክትል መሪው ፓርቲያቸው ኢዜማ ዘመኑን የሚመጥን፣ ኃላፊነት የሚሰማው፣ ከግልና ቡድናዊ ፍላጎትና ጥቅም ይልቅ ሀገራዊና ለትውልድ የሆነ ራዕይ ሰንቆ በኃላፊነት ስሜት የሚንቀሳቀስ በሕግና በሥርዓት በመራመድ ተምሳሌት ሆኖ ለመገኘት እየሠራ ያለ ፓርቲ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለሀገሪቷ ሰላም ከመቼም ጊዜ በላይ ስለሚያስፈልግ የወጣቶች ኮንፍረንስ በማዘጋጀት ወጣቶችን ማሳተፍ እንደሚፈልግ ገልፀዋል፡፡

ምክትል መሪው ሰላም በሰፈነበት ሀገር ዴሞክራሲን ማዋለድ ይቻላል፤ እንደ ዜጋም መበልፀግ ይቻላል፤ ብዙ በጎ ነገሮችንም ለትውልድ ማስተላለፍ ይቻላል ብለዋል፡፡ ወጣትነት ብዙ ሥራ የሚሠራበት ወሳኝ የሆነ የእድሜ ክፍል ነው ያሉት አንዱዓለም አራጌ የዚህ ዘመን ወጣቶች ከአድዋ ድል ከፍ ያለ ዴሞክራሲን የማዋለድ ሥራ መዳፋቸው ውስጥ ወድቆ ይገኛል ብለዋል፡፡ ይህንንም ለመሥራት በሰላም ዙሪያ ቀድሞ መስበክ፣ መምከርና መወያየት ያስፈልጋል ያሉት ምክትል መሪው ፓርቲያቸው ኢዜማም ለዚህ መድረክ ማዘጋጀቱን ጠቁመዋል፡፡

ምክትል መሪው የፊታችን እሁድ መጋቢት 06 ቀን 2012 ዓ.ም የኢዜማ ወጣቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ በአምባሳደር ቲያትር ቤት ያዘጋጀው የወጣቶች ኮንፍረንስ ላይ «ወጣቶች በቦታው በመገኘት የሚጠበቅባችሁን ሁሉ እንድታበረክቱ ከአደራ ጭምር ወንድማዊ ጥሪዬን አቀርባለሁ» ሲሉ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡



# ምርጫ ወረዳ 26/27 ከንዑስ ወረዳ 5 ነዋሪዎች ጋር ውይይት አካሄደ

የዜጎች መድረክ (መጋቢት 03 ቀን 2012 ዓ.ም)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የአዲስ አበባ ምርጫ ወረዳ 26/27 ከንዑስ ወረዳ 5 ነዋሪዎች ጋር በአቃቂ/ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በተለምዶ ውሃልማት ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ባሳለፍነው እሁድ የካቲት 29 ቀን 2012 ዓ.ም ሕዝባዊ ስብሰባ ማካሄዱን የምርጫ ወረዳ 26/27 ምክትል ሰብሳቢ ሠራዊት ጌቶ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

በውይይቱ ላይ የኢዜማ አባል የሆኑ እና አባል ያልሆኑ የወረዳው ነዋሪዎች መሳተፍ መቻላቸውን ምክትል ሰብሳቢው ገልፀዋል ፡፡ውይይቱ የምርጫ 2012 ነባራዊ ሁኔታ መዳሰስን፣ ኢዜማ ለምርጫው ምን ዓይነት ቅድመ ዝግጅት እያደረገ እንደሆነ ማስረዳትንና በወቅታዊ የሀገሪቷ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ መወያየትን ዓላማው አድርጎ መነሳቱን ምክትል ሰብሳቢው ጠቁመዋል፡፡ በውይይቱ ላይ ከተነሱት ዋና ዋና ጥያቄዎች መሀል «ኢዜማ የአማራ ፓርቲ ነው» ይባላል፡፡ ይህን እንዴት ትመለከቱታላችሁ? ኢዜማ ለወጣቶች ምን አስቧል? ለምርጫው እያደረጋችሁት የሚገኘው ዝግጅት ምን ይመስላል? የሚሉት ይገኙበታል ፡፡

«ኢዜማ የአማራ ፓርቲ ነው» በሚል ለተነሳው ጥያቄ በሚመለከት ወሬውን እንደ ጭምጭምታ እንሰማው ስለነበር በተጨባጭ የአባላቶቻችንን መረጃ ይዘን ነበር የቀረብነው ያሉት ምክትል ሰብሳቢው በበምርጫ ወረዳችን ያሉ አባላትን መረጃ በመጥቀስ ጥያቄውን እንደመለሱ እና የኢዜማ ሀሳብ ለማፍረስ ከሚነሱ አሉባልታዎች መካከል እንደሆነ ማስረዳታቸውን ምክትል ሰብሳቢው ገልጸዋል፡፡ ኢዜማ ለወጣቶች ምን አስቧል? በሚል ለተነሳው ጥያቄም ኢዜማ ከአመሰራረቱ ጀምሮ በወጣቶች የሚመራ ፓርቲ መሆኑንና ካዘጋጀው ፖሊሲዎች መካከል አንዱ የወጣቶች ፖሊሲ መሆኑን በመጥቀስ ለወጣቶች ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል ሲሉ ምላሽ እንደተሰጠ አስታውሰዋል ፡፡ለምርጫው እየተደረገ የሚገኘውን ዝግጅት በሚመለከት ለተነሳው ጥያቄም «እኛ ከሌሎች ፓርቲዎች በምን እንደምንሻል የምረጡኝ ዘመቻ ቅስቀሳ ሲጀመር ይታያል፡፡ ምን ዓይነት አደረጃጀት ይዘን እንደመጣን ያኔ የሚታይ ይሆናል፡፡ የገዢው ፓርቲ ሰዎች ራሳቸው እኛን እንደሚመርጡ እርግጠኛ ሆናችሁ ተንቀሳቀሱ» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ነዋሪው በራሱ ተነሳሽነት ይህን ሕዝባዊ ስብሰባ ማዘጋጀቱንና የምርጫ ወረዳውም ምንም ዓይነት ወጪ ሳያወጣ ስብሰባው መካሄዱን ምክትል ሰብሳቢው ገልፀዋል፡፡

የምርጫ ወረዳ 26/27 በጣም ትልቅ የምርጫ ወረዳ እንደሆነና በሥሩም 110 ያሕል የምርጫ ጣቢያዎች እንዳሉት የጠቆሙት ምክትል ሰብሳቢው ምርጫ ወረዳቸው በቀጣይነት ሁለተኛ ቢሮውን ለመክፈት እቅድ እንዳለውና ሁለተኛውን ቢሮ ለመክፈት በማሰብ እየተንቀሳቀሰ እንዳለ አስረድተዋል፡፡

# ኢዜማ የኢኮኖሚ ፖሊሲውን ለንግዱ ማኅበረሰብ ሊያስተዋውቅ ነው

የዜጎች መድረክ (መጋቢት 03 ቀን 2012 ዓ.ም)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የሀብትና ግብዓት አሰባሳቢ ኮሚቴ በአዲስ አበባ ከተማ ለሁለተኛ ጊዜ የገቢ ማሰባሰቢያ ሊያደርግ መሆኑን ለዜጎች መድረክ ገለፀ፡፡

ኮሚቴው የገቢ ማሰባሰቢያውን የሚያካሂደው መጋቢት 19 ቀን 2012 ዓ.ም መሆኑን የገለፀ ሲሆን የገቢ ማሰባሰቢያው የሚካሄድበት ቦታ ቀኑ ሲደርስ የሚገለፅ መሆኑን ኮሚቴው ጠቁሟል፡፡ የገቢ ማሰባሰቢያው ዓላማም የኢዜማን የኢኮኖሚ ፖሊስ ለንግዱ ማኅበረሰብ ማስተዋወቅና ማወያየት መሆኑን ከኮሚቴው ያገኘነው መረጃ ያስረዳል፡፡ የሀብትና ግብዓት አሰባሰብ ኮሚቴ በዚህ የገቢ ማሰባሰቢያ ላይ ቢያንስ 10 ሚሊየን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ መነሳቱን ጠቁሟል፡፡ የገቢ ማሰባሰቢያውን ተከትሎ የተዘጋጀ የራት ፕሮግራም ያለ ሲሆን በራት ፕሮግራሙ ላይ የንግዱ ማኅበረሰብ አባላት ገንዘባቸውን ሲሰጡ ዝም ብለው ከሚሰጡ ምን ጥቅም እንደሚያገኙ አውቀው መስጠት ስለሚኖርባቸው የኢዜማ የኢኮኖሚ ፖሊስ ቀርቦ በፖሊሲው ላይ ውይይት እንደሚደረግ ኮሚቴው ለዜጎች መድረክ ገልጿል፡፡ በፖሊሲ ውይይቱ ላይ የንግዱ ማኅበረሰብ የሚያነሷቸው ሀሳቦች ጠቃሚ ሆነው ከተገኙ እንደ ግብዓት እንደሚወሰዱ ኮሚቴው ጠቁሟል፡፡

የሀብትና ግብዓት አሰባሰብ ኮሚቴ በቀጣይነት የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶችን በመንደፍና የተለያዩ ሰዎችን አሳታፊ በማድረግ በአዲስ አበባም ሆነ ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች ለማካሄድ እየሠራ እንዳለ ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰው መረጃ ያስረዳል፡፡ የሀብትና ግብዓት አሰባሰብ ኮሚቴ ከዚህ ቀደም በአዲስ አበባ ከተማ በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል ታኅሳስ 05 ቀን 2012 ዓ.ም የራት ግብዣ በማካሄድ ገቢ ማሰባሰቡ የሚታወስ ነው፡፡

# < <ኢዜማን በአባልነት እንደ አዲስ የሚቀላቀሉ ሰዎች እጩ ሆነው የሚቀርቡበትን እድል አመቻችተናል> >

**አንዷለም አራጌ የኢዜማ ምክትል መሪ ናቸው:: በተጨማሪነትም የፓርቲው የእጩዎች ምልመላ እና ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ አባል ናቸው:: ኮሚቴው እስካሁን ያከናወናቸውን ተግባራት እና ሥራዎች በሚመለከት ከዜጎች መድረክ ጋር አጠር ያለ ቆይታ አድርገዋል::**



**ከእኛ ጋር አጠር ያለ ቆይታ ለማድረግ ፍቃደኛ ስለሆኑ እናመሰግናለን::**

እኔም በጣም አመሰግናለሁ::

**የእጩዎች ምልመላ እና ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ እንዴትና በምን መልኩ ነበር የተዋቀረው?**

የእጩዎች ምልመላ እና ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ የተቋቋመው ከምርጫ እንቅስቃሴ ጋር በተገናኘ የሚሠሩ ሥራዎችን ለማቀድ፣ ለማሠልጠን፣ ለማስፈፀም፣ እጩዎች ወቅቱን ጠብቆ እንዲዘጋጁ ለማድረግ እንዲሁም እጩዎች የሚመረጡበትን ሁኔታ ለማስቀመጥ ነው:: ለምርጫው ቀድሞ ለመዘጋጀት እና በእኛ በኩል የሚጠበቅብንን ሥራዎች ሠርተን ለመገኘት ያዋቀርነው ኮሚቴ ነው::

**ኮሚቴው የተሰጠው ኃላፊነትና ሚና ምንድን ነው?**

ኃላፊነቱ ሰፊ ነው:: ኢዜማ የሚያስፈልገውን የምርጫ ዝግጅት ለማጠናቀቅ እና በምርጫው ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸውን አባላት እንዲወዳደሩ ሕግ ማውጣት፣ መስፈርቶችን ማውጣትና የወጡት መስፈርቶች በሥልጠና ወጥ በሆነ መልኩ ታች ድረስ እንዲወርድ ማድረግ፣ በወጣው ሕግ መሰረት አባላት ሕጉን ጠብቀው ተወዳድረው (Screen) እንዲደረጉ ማስቻል፣ በየወረዳዎቹ ጠቅላላ ጉባኤ አማካኝነት የሚመረጡትን ሰዎች መከታተልና ሥራዎች በብቃትና በአንድ ማዕከል እንዲሠሩ ማድረግ፣ በየወረዳዎቹ ሁኔታ የተቀናጀ ሥራ መሥራትንና ለሥራዎቹ የሚያስፈልገውን እገዛና ክትትል ማድረግ፣ የሚያስፈልገውን አሰራር ቀድሞ ማሳወቅ፣ ማሠልጠን፣ ክፍተቶችም ካሉ ክፍተቶቹ እየተለዩ እያስተካከሉ መሥራት የኮሚቴው ኃላፊነትና ተግባራት ናቸው::

**መስፈርቶች እንደወጡ ገልፀውልኝ ነበር:: መስፈርቶቹን ማወቅ እንችላለን?**

አዎ:: ዝርዝር መስፈርቶች ነው ያሉት:: የተወሰኑትን ለመግለፅ ያሕል በእኛ ሕግ መሰረት አንድ ሰው ለውድድር ለመቅረብ ከፈለገ አባላት ፊት ንግግር አድርጎ የወረዳውን ጠቅላላ ጉባዔ አሳምኖ መመረጥ ይኖርበታል:: በየወረዳው የተቋቋመ አስመራጭ ኮሚቴ አለ:: ለመመረጥ ፍላጎች ያላቸው ሰዎች ለአስመራጭ ኮሚቴ የታሸገ ማመልከቻ ያቀርቡለታል:: የታሸገው ማመልከቻ ለአስመራጭ ኮሚቴ ከቀረበለት በኋላ በመስፈርቶቹ መሰረት ኮሚቴው እጩዎችን ያወዳድራል::

ከመስፈርቶቹ መሀል የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል የትምሕርት ደረጃ፣ እጩ ተወዳዳሪው/ተወዳዳሪዋ በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለው/ያላት ተቀባይነት፣ የሥራ ልምድ፣ ስነምግባር፣ ከዚህ ቀደም በፖለቲካ ያለው ልምድ፣ የፓርቲው መመዘኛ የሆኑትን የአባልነት ግዴታዎች በአግባቡ ተወጥቷል ወይ? የሚሉ መመዘኛዎች እንደ መስፈርት የተቀመጡ ናቸው:: እነዚህ ሁሉ መስፈርቶች እያንዳንዳቸው ነጥብ ይሰጣቸዋል:: እነዚህ ሁሉ ተደምረው ከ1 እስከ 4 ተከታታይ ውጤት ያመጡ ሰዎች የሚያልፉ ይሆናል:: አራቱ ዕጩዎች ከ50 በመቶ በላይ ድምፅ ያላመጡ ከሆነ ከአራቱ መሀል ከፍተኛ ውጤት ያመጡት ሁለቱ እንደገና ምርጫ እንዲያደርጉ ይደረጋል:: ከሁለቱ ከቀሩት ውስጥ አንደኛዋ ሴት ከሆነችና በነጥብ የምትበልጠው ከሆነ እንደገና ምርጫ ሳይካሄድ ሴቷ እንድታልፍ ይደረጋል:: ወንዱ የቀረችውን እጩ ሴት ተወዳዳሪ በነጥብ የሚበልጣት ከሆነና የሚበልጣት የነጥብ ልዩነት ከ10 በላይ ካልሆነ አሁንም ቅድሚያ የሚሰጠው ለሴቷ ነው:: በወንዱ እና በሴቷ እጩ ተወዳዳሪ መሀል ያለው ልዩነት ከ10 ከበለጠ (ለምሳሌ ያሕል በ11 ነጥብ) የሚበልጣት ከሆነ ግን በድጋሚ ለምርጫ የሚወዳደሩ ይሆናል:: መስፈርቶቹ በውስጣቸው በጣም ደስ የሚሉ ነገሮችን ነው የያዙት:: ዴሞክራሲን በተግባር ለመለማመድ የምንሞክርበት በጣም ብዙ መስፈርቶች ነው ያሉን::

**መስፈርቶቹ ምን እንደሚመስሉ ለማስረዳት ሞክረዋል:: እነዚህ መስፈርቶች ምን ዓይነት እጩዎችን ያመጡልናል ብላችሁ ታስባላችሁ?**

በተቻለ መጠን እነዚህ መስፈርቶች ከአባላቶቻችን ውስጥ ሕዝቡ የሚያከብረውን፣ በተሻለ የሚሠራውንና ፓርቲያችንን በተሻለ የሚወክለውን ሰው እጩ ሆነው ከሚቀርቡት ሰዎች መሀል ለመለየት ይረዳናል ብለን ነው የምናስበው:: ይህንን ሙከራችንን በበርካታ ወረዳዎች ላይ እያደረግነው ነው:: በአሁኑ ወቅትም አስመራጮችን እየመረጥን ነው:: በዚህ ሂደት ውስጥ ሕዝቡንም ሆነ አባላቶቻችንን ከወሬ በዘለለ በተግባር የዴሞክራሲ ባሕል ምን ማለት እንደሆነ እያሳየን እንገኛለን:: የሀገሪቱን 65 በመቶ ክፍል በመሸፈን በኢትዮጵያ ደረጃ ከ400 በላይ ወረዳዎች ላይ ይህንን ለመተግበር መሞከር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረግ ነው:: ኢዜማ ውስጥ ባደረኩት አስተዋፅኦ ከምደሰትባቸው ነገሮች አንዱ ይህ ነው:: ሰው ላያየው ይችል ይሆናል፤ ጭብጨባም ላያስገኝ ይችላል:: ነገር ግን በተግባር የሚሠራው ነገር በጣም አስፈላጊ ነው::



> " ከተወዳዳሪዎቹ የተሻለ ቁጥር ያላቸው ሴቶች በተቻለ መጠን እንዲወዳደሩ ለማድረግና እንዲያልፉ ነው የምንፈልገው:: ለክልል ምክር ቤት የምናቀርባቸው ዕጩዎች ውስጥ ቢያንስ 30 ከመቶ ተወዳዳሪዎቻችን ሴቶች ናቸው የሚሆኑት:: "

**ሴቶች 51 በመቶ የሚሆነውን የማኅበረሰባችንን ክፍል ይይዛሉ:: ይህ ኮሚቴ በዚህ ሂደት ውስጥ ሴቶችን ምን ያሕል ተሳታፊ አድርጓል? ሴቶችን**

**ተሳታፊ አድርጎ ከሆነም ጥቂት ይበሉን፡፡**

ለምሳሌ ትምሕርት ደረጃ በሚያስቀምጠው መመዘኛ መስፈርት ላይ ለወንድ 30 ነጥብ ይዘን ከሆነ ሴቷ በ25 እንድታልፍ እናደርጋለን፡፡ ፒኤችዲ ያለው ወንድ 35 በመቶ ነጥብ ከሰጠነው ሴት ሆና ማስተርስ ካላት 35 ነጥብ እንዲሰጣት ይደረጋል፡፡ ወንድ ሆኖ ማስተርስ ዲግሪ ካቀረበ 30 ከመቶ ከሰጠነው ሴቷ ቢ.ኤ ዲግሪ ካቀረበች 30 በመቶ ይሰጣታል፡፡ ወንድ ሆኖ ቢኤ ዲግሪ ካቀረበ 25 ከመቶ ከተሰጠው ሴቷ ግን ዲፕሎማ አቅርባ 25 ከመቶ እንዲሰጣት ይደረጋል፡፡ ሴቶችን በዚህ መልክ ለማሳተፍ እና እጩ ሆነው እንዲቀርቡ ለማበረታታት ጥረት አድርገናል፡፡ ከተወዳዳሪዎቹ የተሻለ ቁጥር ያላቸው ሴቶች በተቻለ መጠን እንዲወዳደሩ ለማድረግና እንዲያልፉ ነው የምንፈልገው፡፡ ለክልል ምክር ቤት የምናቀርባቸው ዕጩዎች ውስጥ ቢያንስ 30 ከመቶ ተወዳዳሪዎቻችን ሴቶች ናቸው የሚሆኑት፡፡

**የእጩዎች ምልመላና ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ እስካሁን ባካሄዳቸው ምልመላዎች ለተወካዮች ምክር ቤትም ሆነ ለክልል ምክር ቤት ኢዜማን ወክለው የሚወዳደሩ በቂና አቅም ያላቸውን እጩዎች አግኝቷል ማለት ይቻላል?**

በየወረዳው እና በየዞኑ ወርደን ለተወካዮች ምክር ቤት እና ለክልል ምክር ቤት ምን ያሕል ሰው ተመዝግቧል የሚለውን በማጣራት ላይ ነው የምንገኘው፡፡ ያልጠበቅናቸው ቦታዎች ላይ ከጥራትም ሆነ ከብዛት አንፃር በጣም ብዙ እጩዎችን ያገኘንባቸው ቦታዎች አሉ፡፡ ችግር አይገጥመንም ብለን ያሰብናቸው ቦታዎች ላይ ሳስቶ ያገኘንባቸው አጋጣሚዎች ተፈጥረዋል፡፡ ሂደቱን ቀድመን ነው የጀመርነው፡፡ ቀድመን መጀመራችን ነገሮችን ተመልሶ ለማጥራት እድል ይሰጠናል፡፡ ይህንን ታሳቢ በማድረግ አባላት ላይ ጫና ፈጥረን ነበር፡፡ የማመልከቻ ጊዜው ስላላበቃ የመጨረሻ ስእል የለንም፡፡ ነገር ግን በብዙ ቦታዎች ላይ የሚያበረታታ ነገር ማስተዋል ችለናል፡፡

**ኮሚቴው ሥራውን አሁንም ድረስ እየሠራ እንዳለ ነው የገለፁልን፡፡ ባለን መረጃ የእጩዎች ምልመላ እስከ መጋቢት 14 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ የሚዘልቅ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ እስካሁን ኢዜማን ያልተቀላቀሉ ሰዎች ኢዜማን ተቀላቅለው እጩ ሆነው የሚቀርቡበት እድል አለ?**

አዎ፡፡ እንደምታውቁት ፓርቲያችን ከተመሰረተ ገና አንድ ዓመት እንኳ አላስቆጠረም፡፡ ስለዚህ አንዳንዶቹ ሕጎቻችን የወደፊቱን ጊዜ ታሳቢ ተደርገው የተሠሩ



> “አንዳንዶቹ ሕጎቻችን የወደፊቱን ጊዜ ታሳቢ ተደርገው የተሠሩ ናቸው፡፡ ፓርቲያችንን በደንብ አቋቁመን ሳንጨርስ ነው የምርጫ ጉዳይ የመጣው፡፡ ሰዎች ፓርቲያችንን ገና በመቀላቀል ላይ ናቸው፡፡ አዳዲስ ሰዎችንን እየመዘገብን ነው ያለነው ”

ናቸው፡፡ ፓርቲያችንን በደንብ አቋቁመን ሳንጨርስ ነው የምርጫ ጉዳይ የመጣው፡፡ ሰዎች ፓርቲያችንን ገና በመቀላቀል ላይ ናቸው፡፡ አዳዲስ ሰዎችንን እየመዘገብን ነው ያለነው፡፡ በስብስብም ሆነ በግለሰብ ደረጃ የሚመጡ ሰዎች የመወዳደር መብት ሊሰጣቸው ይገባል ብለን እድል ሰጥተናል፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተቋቋምን ፓርቲ መሆናችንን ግንዛቤ ውስጥ ከተን እድሉን ለሰዎች እንዳናጣብብ በማለት አዲስ የሚመጡ ሰዎችም የመወዳደር ፍላጎት ካላቸው እና ፎርሟሊቲውን ተከትለው በወረዳቸው የተመዘገቡ እና የአባልነት መዋጮዋቸውን የሚወጡ እስከሆነ ድረስ እጩ ሆነው የሚቀርቡበትን እድል አመቻችተናል፡፡

**ኢዜማን ዘግይተው የተቀላቀሉ አባላት ኮሚቴው ያወጣቸውን መስፈርቶች እስካሟሉ ድረስ እጩ ሆነው የሚቀርቡበት እድል አለ ብንል አልተሳሳትንም ማለት ነው?**

አዎ፡፡

**እንደ ኮሚቴው አባልነትዎ የሚያስተላልፉት ጥሪ ካለ ጥሪዎን አስተላልፈው ቃለምልልሱን እዚህ ላይ እንደምድመው፡፡**

ዴሞክራሲ እንዲወለድ እንፈልጋለን፡፡ ትልቁ ሕልማችን እንደ ትውልድ ዴሞክራሲን ማዋለድ ነው፡፡ ቅድሚያ የምንሰጠውም ለእሱ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በሥነምግባርም አርአያ ሆነን በመታየት ተምሳሌታዊ ሥራ መሥራት እንፈልጋለን፡፡ በተቻለ መጠንም ይህንን ለማድረግ በመሞከር ላይ እንገኛለን፡፡ ሰውም እየተረዳን ነው ብለን እናስባለን፡፡ ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት አሁን እየሠራን ያለነው (የእጩዎች ድጋፍና አስተባባሪ ኮሚቴ እየሠራ ያለው) ለሰዉ የሚታይ ባይሆንም ጥሩ የሆነ የዴሞክራሲ ልምምድ በፓርቲያችን ውስጥ እያደረግን ነው ያለነው፡፡ በዚህ ሂደት የሚገጥሙንን አባጣና ጎርባጣ ነገሮችን እያስተካከልን ለእኛ ሳይሆን ለትውልድ የሚቀጥል ትልቅ ፓርቲ ለመፍጠር እየሠራን ነው፡፡ ለእኛ ሳይሆን ለትውልድ የሚተርፍ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲፈጠር የበኩላችንን ለማድረግ እየሠራን ነው ያለነው፡፡ ሁሉም ወገኖች እንዲረዱን እንፈልጋለን፡፡ ከጎንዮሽ መነቋቆርና ከታወረ የግል ነገር ይልቅ ሀገራችንን ከፍ አድርገን እንድንመለከትና ዋናው ስእል ላይ አተኩረን የሚወለደውን ዴሞክራሲ እንዴት ተባብረን እናዋልደው? ለልጆቻችን እንዴት የተሻለ ሀገር እናስተላልፍላቸው? ልጆቻችን የማይሰደዱበት የሚኮሩበት ለሌሎችም አይን ማረፊያ የሆነ ሀገር አውርሰን እንዴት በክብር እንሸኝ? የሚለውን ሀሳብ ሁሉም ፓርቲዎችና የሚመለከታቸው ኢትዮጵያውያን ወገኖች ተቀዳሚ ሀሳባችን አድርገን በዛ ዙሪያ ብንሰራ መልካም ነው፡፡

በመንግሥት በኩልም ከሚጠበቀው የወረዱ አሰራሮች በየአጋጣሚውና በየአካባቢው እየገጠሙን ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች በጣም መታረም አለባቸው፡፡ እኛ የምናስበው ስለትውልድና ስለሚመጣው ዘመን ነው፡፡ መንግሥትም ይህ ሊያሳስበው ይገባል፡፡ ከዚህ ቀደም ብዙ ቃል ሲገቡ ሰምተናል የገቡትን ቃል እንዲያከብሩ አደራ እንላለን፡፡ ወደማንፈልገው መንገድ እንዳይገፉን አደራ ለማለት እንወዳለን፡፡ ፓርቲዎችም በኃላፊነት ስሜት በመንቀሳቀስና እንደ ትውልድ አንድ ዓላማ እንሰንቅ፡፡ ዓላማችን ላይ ተረባርበንም በኋላ ላይም በሕዝብ ፍቃድ የተመረጠ ሰው እንዲያገለግል እና በሂደትም እየተፈራረቅን ሀገራችንን የምናገለግልበት ሁኔታ የሚፈጠርበት መደላድል እንዲነጠፍ ሁላችንንም ለዚህ የሚገባንን እንድናደርግ አደራ ለማለት እወዳለሁ፡፡



